# እንደ ሰው መሬቱ

ህዳር 2002

abraham beyenne

ሺህ ህይዎት መርገፉ - በርሃብ ተጠብሶ
ለሱዳን ድንበሩ - መሄዱ ተቆርሶ
ገበሬው ተነጥቆ - ባለቤትነቱ
ጭራሽ ተፈናቅሎ - ከቀየው ከርስቱ
ለቻይና ለኮሪያ ለሳዑዲ..... መሬቱ
ለህንድ መሸጡ - በደሉ ሳያነሰው
በሠራተኝነት -ጉልበቱን መዝብሮ
በአበባ ኬሚካል - አፈሩን አሳርሮ
ያዘመረው ሰብል - እውቂያኖስ ተሻግሮ
ሲጓጓዝ አዝመራው - ሕዝብ አስርቦ ምርቱ
የሞት ሳል ይስላል- እንደ ሰው መሬቱ።
የውርቁም ማዕድን - ደግሞ እንደ መሬቱ
የህፃናቱ ንግድ - ገበያው መድራቱ
የሴቶቹ ሽያጭ - የባሪያ ፍንገላው
የሥራ አጡ ብዛት - የጫት ቤት መዋያው
የዕስረኛው መከራ - ስቃዩ ስየሉ
ስብዕናው ተፍቆ - በግፍ መገደሉ
ርዕስ እንዳይሆን - የሕዝብ መወያያ
ኮሾ ተቀዋሚ - በወያኔ ጉያ
ገብቶ ለመወሸቅ - በስመ ፓርላማ
በሥነ ምግባር ህግ - ባፀደቀው ፊርማ
ተቃዋሚነት ነው - ድርጅት በርክቶ
አትራፊ የሆነው - ንግዱ ገበያው ደርቶ።
ለዚህ ሁሉ በደል - ሥርየት ፍለጋ
ከተማ እስከ ገጠር - ከቆላ እስከ ደጋ
ሕዝብ ተነቃንቆ - እንዳያምፅ አገር

ሥራ ማቆም አድማ - ሰልፍ ብሎ ነገር
ማሰቡ እንዲያሳስር - እንኳን ተተግብሮ
በሥነ ምግባር ህግ - ተጠርንፎ ታስሮ
ፍትሁ ተድጦ - መብቱ ተገትቶ
አገር ባፈላማ - ህዝብ አለ ታግቶ።
እንደ አሽዋ ደቆ - መፈጨት መቀጥቀጥ
በደል አስመርሮት - በርሃብ መርመጥመጥ
ግፉ ሞልቶ ሲፈስ - ህዝብ አምርሮ ሲቆርጥ
ዐመፅ አቀጣጥሎ - ሲነሳ ገንፍሎ
ይብላኝ ለባለፅዳ - ቀን ሲሄድ ዘንብሎ!!!!
ህዳር 2002
abraham beyenne